# 1. መልክእ

## 1.1. መልክእ ምንድን ነው?

«መልክእ» የግእዝ ቃል ሲሆን «ለክአ» ከሚለው ግስ የወጣ ነው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ «ለክአ» ማለት «ጣፈ፣ ዐተመ፣ ሣለ መሰለ፤ መልክ አወጣ፤ በቀለም በቅርጽ» /1948፣565/ ነው በማለት መልክእን በቁሙ፣ መልክ፣ ገጽ፣ የፊት ቅርጽ፣ ሥዕል ምስል፣ ልክ ያለው በልክ የተሠራ» /1948፣ 566/ በማለት ይፈቱታል። ስለዚህ መልክእ በጥሬ ፍችው ለግዙፍ ነገር ማለት ለሰዎች ወይም ለእንስሳት የሚነገር ይሆናል፤ ብዙ ቁጥሩም መልክአት ነው።

ሌላውና ለዚህ ጽሑፍ ተስማሚው የቃሉ ፍቺ ለግእዝ የሥነ ግጥም ዓይነት የተሰጠው ስም መሆኑ ነው። በዚህ ረገድ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ሆነ ከዘመናዊ ምሁራን ከተሰጡት መካከል አሟልቶ ያልያዘው ነገር ያለ ይመስለኛል። ከሁለቱም ክፍሎች ሁለት ሁለት ፍቺዎችን እንመልከት።

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /1948፣ 566/ መልክእ የድርሰት ስም፣ የመልክ ውሳኔና መዝሙር፣ ከራስ ጠ ጉር እስከ እግር ጥፍር የሚቆጥር ይሉታል። ይህ ፍቺ በብዙ የቤተ ክርስቲያንም ሆነ ዘመናዊ ሊቃውንት ተቀባይነት ያገኘ ነው። አለቃ አያሌው ታምሩ እነዚህ ግጥሞች የባለመልክኡን መልክ ከስሙ በመጀመር ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በቅደም ተከተል በስንኝ የሚያመሰግኑ ናቸው። /1992/ ይላሉ። እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የአለቃ አያሌውም ፍቺ የመልክእን ዋና ዋና ባሕርያት ማለት ገላጭ መሆኑን፣ የሰውነት አካላትን መዘርዘሩን፣ ምስጋና መሆኑንና በስንኝ መጻፉን ይጠቅሳሉ። በነዚህ ሁለት ፍቺዎች መካከል ያለው ልዩነት የመልክእን የምስጋና መጀመሪያ ክፍል በመጥቀስና ባለመጥቀስ ነው።

ፖላንዳዊው ምሁር አሌክሳንደር ፌሬንክ /1985፣ 283/ መልክእን ሲፈታው «የባለመልክኡን የተለያዩ የሰውነት አካላት በአብዛኛው ከራስ ጀምሮ እስከ እግር ድረስ የሚያመሰግን ገላጭ ግጥም ነው» ይላል። ይህ የፌሬንክ ፍቺም ከላይ ከጠቀስናቸው የቤተ ክህነት ሊቃውንት ፍቺዎች ጋር የተመሳሰለ ነው፤ ከጥቂት ልዩነቶች በቀር። ፌሬንክ መልክእ የሚጀምረው ከራስ ነው በማለት ስምንና ፀጉርን ሳይጠቅስ ያልፋቸዋል። ሌላው ሀርደን /1926፣29/ የተባለ ምሁር «መልክእ የእያንዳንዱን ቅዱስ የሰውነት አካል እየዘረዘረ በአንዳንድ አርኬ የሚመሰገንበት መዝሙር ነው» ይላል። ይህ ፍቺ የሰውነት አካላት በቅደም ተከተል ስለመመስገናቸው አይናገርም። እርግጥ ብዙ አርኬዎች ያሉት መሆኑን ይጠቅሳል፤ አንድ አርኬ ለአንድ የሰውነት ክፍል በማለት ቢሳሳትም በተጨማሪም መልክእ የሚጻፍላቸው ቅዱሳን ብቻ እንደሆኑ ያስመስላል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የመልክእ ፍቺዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ባለ መልክኦቹ የተለያዩ ብልቶች ያላቸው ግዙፍ አካል እንደሆኑ ይጠቅሳሉ። ግዙፍ አካላት የሌላቸው መልክእ የተጻፈላቸው አሉ። ከእነዚህ ግዙፍ አካል ሳይኖራቸው መልክእ ከተጻፈላቸው ውስጥ ንዋያተ ቅድሳት፣ የጸሎት መጻሕፍትና ልዑል እግዚአብሔር ይገኙበታል። ለምሳሌ ያህል ጠቢበ ጠቢባንን፣ መልክአ መስቀልን፣ መልክአ ሰንበትን፣ መልክአ አንቀጸ ብርሃንን መጥቀስ ይቻላል።
ስለዚህ መልክእ ማለት የባለመልኩን የሰውነት አካላት እና/ወይም ሌሎች ነገሮችን በማመስገን ምሕረትን የሚለምን ባለብዙ አርኬዎች የምስጋና ግጥም ነው።

## 1.2. መልክአ መልክእ የተጀመረበትና የቆመበት ዘመን

መልክአ መልክእ መጻፍ የተጀመረበትን ጊዜ በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም። እኔ እስከማውቀው ድረስም ይህንኑ በእርግጠኛነት የተናገረ ተመራማሪ የለም።

መልክአ መልክእ መድረስ የጀመሩበትን ሳይሆን በስፋት የተጻፉበትን ዘመን 17ኛው ምእተ ዓመት የሚያደርጉ አሉ። /ፌሬንክ፣ 1985፣ 285/። ዓለማየሁ ሞገስ /1952፡4/ ወደ 14ኛ ምእተ ዓመት ይወስዱታል። እንደ ፔደርሰን /1989፡557/ ያሉት ደግሞ መልክእ እስከ 17ኛ ምእተ ዓመት ድረስ እንዳልተጀመረ ይናገራሉ። የዚህ ሁሉ ልዩነት መነሻው ድርሰቶቹ በተጻፉበት ብራና ላይ ጊዜን የሚጠ ቁም ምንም ነገር አለመገኘቱ ነው።

«እግዚአብሔር መልክ አለው ወይስ የለውም» የሚለው ጉዳይ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ጊዜ ያወዛገበ ነገር ነበር። /ሩንግሬን፣ 1982፣ 59/። ደቀ እስጢፋ የተባሉ የድንግል ማርያምን፣ የመላእክትን፣ የቅዱሳንንና የጻድቃንን ከእግዚአብሔር የማግለድ ጉዳይን ያልተቀበሉት በዚያው ዘመን የተነሡ ነበሩ። እነዚሁ ሰዎች

ለቅዱሳንና ለሥዕለ አድኅኖ ክብር የሚሰጠውን ስግደትም ይቃወሙ ነበር። ይህ የደቀ እስጢፋ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ኑፋቄ ነው ተብሎ በንጉሡ ፍርድ የከፋ ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል።

ይህ ውዝግብ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን የምልጃን ኃይልና ለቅዱሳንና ለሥዕሎቻቸው መስገድን የሚያረጋግጡበትን አዲስ የግእዝ ግጥም ስልት እንዲያስገኙ ግፊት የሆናቸው ይመስላል። ይህ መላምት እውነት የሚመስለው በዚያ ዘመን ይህን ኑፋቄ የሚቃወሙ ብዙ ሃይማኖታዊ ጽሑፎች በመውጣታቸው ነው። የሚከተለው አርኬ የዚህን ኑፋቄ ችግር ያነሣል።

**ሰላም ሰላም ለመልክአ ሥዕልኪ ኩሉ**
**እምነ ፀሐይ ወወርኅ ዘያበርህ ሥነ ፀዳሉ**
**ወበእንተዝ ማርያም ሰብአ ቤትኪ ይብሉ**
**ስብሐት ወክብር ወሰጊድ ለመንግሥት ይደሉ**
**ማርያም በረከትኪ ምስሌነ የሀሉ። /መልክአ ሥዕል፣ አርኬ 23/**

ይህ አርኬ ለቅድስት ድንግል ማርያም መስገድ ተገቢ መሆኑን ይናገራል። የሚከተለውም ስንኝ ይህንኑ ኑፋቄ በቀጥታ ያወግዛል።

**ሰላም ለማርያም ዐጽፈ ወልድ ዋሕድ**
**ወመንበረ ሕያው ነድ**
**ለድንግልናሃ ይደሉ ሰጊድ**
**ለማርያም ዘይቤ ኢይስግድ**

ሞጸፈ መብረቅ በሊኀ በርእሱ ለይረድ /መልክአ ሥዕል ዳግሚት፣ አርኬ 1/

ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ሁለት አርኬዎች የስግደትን ተገቢነትና ስግደትን መቃወም ኑፋቄ እንደሆነ የሚያስረዱ ናቸው። ሌላው ይህን መላምት የሚደግፈው በየገድላቱ መጨረሻ ወይም መጀመሪያ መልክእን መጨመር ልማድ መሆኑ ነው። ገድላት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት መጻፍ እንደተጀመሩ ይነገራል። /አምሳሉ፣ 1976፡54/። ስለዚህ መልክእም በዚያው ጊዜ መገጠም ጀመሮ ሊሆን ይችላል። የሆነው ሆኖ ይህ ጉዳይ የብራናዎቹን ጥልቅ ጥናት የሚሻና የባለመልክአቹን ታሪክ ማጥናትን የሚጠይቅ የምርምር መስክ ነው።

## 1.3. ደራሲ

የሁሉም መልክአ መልክእ ደራሲዎች /በአብዛኛው/ አይታወቁም። እያንዳንዱ የመልክእ ደራሲ በድርሰቱ ውስጥ የራሱን የተለየ የአጻጻፍ ስልት ስለማይጠቀም ይህ ጉዳይ ብዙም ችግር አይሆንም። የሥነ ቃል ደራሲው አይታወቅም ደራሲያቸውን ልዩ ስልት ሳይጠቀሙ ራሳቸውን ሆን ብለው ያልጠቀሱ በመሆናቸው ነው።

የመልክአ መልክእ ደራስያን እንደ ባለቅኔዎች አካባቢን በመከታተልና በምናብ ምጥቀት አይታወቁም። /አያሌው፣ 1992/። አንደ ተማረና ጥሩ መናገር /መጻፍ/ እንደሚችል ሰው እንጂ። የመልክእ ክብሩ በደራሲው ታላቅነት ሳይሆን በባለመልክኡ ታላቅነት ነው። በመልክአ መልክእ ውስጥ የሠፉሩት የአንድ ሰው ስሜትን የያዙ ሳይሆኑ ለሁሉም ሰው የሚሆኑ ምስጋና፣ ኑዛዜ፣ ምሕረትና ልመናን የያዙ ናቸው።

የመልክአ መልክእ ደራስያን የአጻጻፍ ልማድን ተከትለው የሚጽፉ ናቸው። ደራስያኑ የሚጽፉበት ርእሰ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአጻጻፍ ስልቱም የሚይዙት ስሜትም ተወስኖ የተሰጣቸው ነው። አንድ ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱ ካደገ በኋላ የመልክእ ቅርጽ እንደ ሕግ ተይዞ ተከታዮቹ እንዲከተሉት ሆኗል። ስለዚህም ግላዊ የሆነው ስሜታቸው በሚጽፉት መልክእ ውስጥ ሊገለጽ አይችልም። ዋና ጉዳያቸው ያጻጻፍ ሥርዓቱን ተከትለው መጻፍ ነው። በአጠቃላይ መልክአ መልክእ ግልጽ የአጻጻፍ ስልት ያለው የአካላት ገለጻ ነው። ስለዚህም ሊነበቡ የሚገባቸው በማስተዋል ነው።

መልክአ መልክእ ለጸሎትነት የሚያገለግሉ ግጥሞች ናቸው። ምሕረትን የሚለምኑትም ደራሲዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ጸሎተኛው ራሱን በደራሲው ቦታ ተክቶ እኔ እያለ ይናገራል። ይህ ራስን በደራሲው ቦታ ማስቀመጥ ደራሲውን ከአንባቢው አእምሮ ያርቀዋል። ይህም ጸሎተኛው የሚያቀርበው የምስጋናና የልመና ጸሎት የራሱ አድርጎ እንዲቆጥር ያደርገዋል። ይህን የሚያስረዳ ምሳሌ ልስጥ።

**ማኅበረ ምእመናን ወምእመናት እለኪያከ ተአመኑ**
**ለነሚአ ሥጋከ ወትረ ኅበ ተፀየኑ**

**ወልደ አብ ክርስቶስ ዘኢትትፌለጥ እም ሕፅኑ**
**እሰብክ ሎሙ ሕማመከ ወመስቀልከ እዜኑ**
**ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሊተ እምሰማይ ፈኑ።**
**/መልክአ ቁርባን፣ አርኬ 1/**

ይህ ግጥም የሚደገመው በካህናት ሲሆን ካህኑ ሁሉ ራሱን በደራሲው ቦታ እንዲተካ የሚያደርግ ነው።

## 1.4. ባለመልክእ

ባለመልክኦቹን በሚመለከት እስካሁን የተጻፉት መልክአ መልክእ በአራት ይከፈላሉ።

### ሀ. እግዚአብሔር

ለእግዚአብሔር /ሥላሴ/ የተጻፉ መልክአ መልክእ አሉ። ለምሳሌ መልክአ እግዚአብሔር አብ፣ ጠቢበ ጠቢባን፣ መልክአ ጰራቅሊጦስና መልክአ ሥላሴ ይጠቀሳሉ።

### ለ. መላእክት

ለመላእክት የተጻፉ ብዙ መልክአ መልክእ አሉ። እነዚህን ለሁለት መክፈል እንችላለን፤ በወል ስም የተጻፉና ለእኔ ባይ የተጻፉ። የወል ስም ለተሰጣቸው መላእክት የተጻፉ እንደ መልክአ ዑቃቤ መልአክ እና መልክአ መላእክት ያሉ፤ እኔ ባይ ሊሆኑ የተጸውኦ ስም ላላቸው መላእክትም በስማቸው መልክአ መልክእ የተደረሰላቸው ሲሆን ለምሳሌም መልክአ ሚካኤልንና መልክአ ገብርኤልን መጥቀስ ይቻላል።

### ሐ. የሰው ልጆች

ለቅዱሳን፣ ለሰማዕታትና ለጻድቃን የተጻፉ ብዙ መልክአ መልክእ አሉ። እነዚህንም እንደላይኛው ለሁለት መክፈል እንችላለን። የወል ስም ያላቸው እንደ መልክአ ሰማዕታት፣ መልክአ ነቢያት፣ መልክአ ጻድቃን፣ መልክአ ሠለስቱ ምእትና የመሳሰሉት ናቸው። እኔ ባይ የተጸውኦ ስም ለተሰጣቸው የተጻፉ አሉ፤ መልክአ ጊዮርጊስ፣ መልክአ አዳም፣ ...። ከዚህም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ጻድቅ ናቸው ተብለው ላልተከበሩ ነገሥታትም መልክእ ተደርሶላቸዋል። መልክአ አፄ ተዎድሮስ፤ መልክአ አፄ ዮሐንስ፣ መልክአ አፄ ምኒልክና የመሳሰሉት።

### መ. ረቂቅና ሕያው ያልሆኑ

ለረቂቅ ሐሳቦችና ሕያው ላልሆኑ ግዑዝ ነገሮች መልክአ መልክእ ተጽፎ እናገኛለን። ረቂቅ ሐሳቦች ማለት እንደ ፍቅር፣ ባሕርይና ጠባይ ሲሆኑ ለነዚህ መልክአ ፍቅር፣ መልክአ ባሕርይ፣ መልክአ ጠባይ፣ መልክአ ሰንበት የሚሉ መልክአ መልክእ ተጽፈውላቸዋል። ሕያው ያልሆኑ ነገሮች ያልኳቸውም ንዋያተ ቅድሳት፣ የጸሎት መጻሕፍትና የመሳሰሉት ሲሆኑ በዚህ ክፍል መልክአ አንቀጸ ብርሃን፣ መልክአ ሥዕልና መልክአ ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

አንዳንድ ባለመልክእ ግዙፍ አካልና ሰብአዊ መልክእ ባይኖራቸውም እንዳላቸው ተደርጎ በሰውኛ ተጽፎላቸዋል። ለምሳሌ መልክአ ቤተ ክርስቲያን፣ መልክአ ፍቅር እና መልክአ ሰንበት ሰብአዊ አካል እንዳላቸው ተደርጎ ተጽፎላቸዋል።

በቤተ ክርስቲያን በልዩ ክብር የሚታዩ አንዳንድ ባለመልክአ መልክእ በስማቸው የተለያዩ ብዙ መልክአ መልክእ ተደርሶላቸዋል። ለምሳሌ የባለመልክኡን ልዩ በዓላት በማሰብ መልክአ መልክእ ይጻፋል። ለምሳሌ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለድንግል ማርያም የተደረሱትን እንመልከት።

## 1.5. መልክአ መልክእና ቅዳሴ

ለኢየሱስ ክርስቶስ ለድንግል ማርያም
1. መልክአ ኢየሱስ 1. መልክአ ማርያም
2. መልክአ ዐማኑኤል 2. መልክአ ኤዶም
3. መልክአ መድኃኔዓለም 3. መልክአ ፍልሰታ ለማርያም
4. መልክአ መድኃኔዓለም እሰግድ 4. መልክአ ቁስቋም
5. መልክአ ቁርባን 5. መልክአ ሥዕል

6. መልክአ መስቀል 6. መልክአ ኪዳነ ምሕረት
7. ልሳነ ሰብእ 7. መልክአ ልደታ ለማርያም
8. መልክአ ቅንዋት 8. መልክአ ልደታ ለማርያም ጻግሚት
9. መልክአ ማኅየዊ 9. መልክአ ማርያም ካልእ
10. መልክአ ማርያም ሣልሲት
11. መልክአ ድንግል
12. መልክአ ጎልጎታ
13. መልክአ በኣታ

ቅዳሴ መሥዋዕት፣ ጸሎትና የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የሚከናወኑበት ሥርዓት ጸሎት ነው። ሥጋ ወደሙን ካህናት ለምእመናን ከማቀበላቸው በፊትና በኋላ መልክአ ቁርባንን ይዘምሩታል። መልክአ ቁርባን የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚያከብር መልክእ ነው።

ከቅዳሴ በኋላ በየዕለቱ ከሚደገሙ ጸሎታት ውስጥ ከውዳሴ ማርያም ጋር የሚጸለዩት መልክአ ማርያምና መልክአ ኢየሱስ ይገኙበታል፤ እነዚህ መልክአ መልክእ በካህናቱ ይደገማሉ። ይህ ጸሎት የሚካሄደው መልክኡ እስኪፈጸም ድረስ በቅደም ተከተል ለካህናቱና ለሊቃውንቱ አንዳንድ አርኬ በማደል ነው። ማደሉ የሚካሄደው በዲያቆናት ወይም በሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሲሆን የሚጠቅሱት እያንዳንዱ አርኬ የሚያመሰግኑትን የመጀመሪያውን የሰውነት አካል ወይም ሌላ ቃል ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ዕለቱ መታሰቢያው የሆነ ጻድቅ፣ ሰማዕት፣ መልአክ ወይም ሌላ በዕለቱ ከተጠቀሱት መልክአ መልክእ በተጨማሪ የእርሱ መልክእም ይደገማል። ቤተ ክርስቲያኑ የሚታሰብበትን ስም የያዘው መልክእ ወይም ጻድቅ ስምም በዚያ ቤተ ክርስቲያን መልክኡ በየዕለቱ ይደገማል። ለምሳሌ በላሊበላ መልክእ ላሊበላ እና በሳማ ሰንበት ደግሞ መልክአ ሰንበት በየቀኑ ይደገማሉ።

መልክአ መልክእ በዜማ ሊዘመሩ ይችላሉ። የሚዘመሩትም ከመልክኡ ውስጥ ተመርጠው የወጡ ጥቂት ስንኞች ናቸው። የሚከበረው ዕለት የሚታሰብበት መልክእ ወይም ጻድቅ … በዓመታዊ ክብሩ ዕለት ከመልክእ ውስጥ ጥቂት ስንኞች ተመርጠው በጸናጽል፣ በከበሮ ይዘመራሉ። ለምሳሌ ለልደት በዓል ከመልክአ ኢየሱስ ሁለት አርኬዎች ይዘመራሉ፤ አርኬ

## 1 እና አርኬ 28።

መልክእ እንደ ጸሎት መጽሐፍ ከማገልገሉ በተጨማሪ የማስተማር ተግባርንም ያከናውናል። የባለመልክኡን ሕይወትና ተአምራት ከጸሎተኛው ጋር ያስተዋውቃል። ይህን የሚያደርገውም መልክአ የተመሠረተው በባለመልክኡ ታሪክ ላይ በመሆኑ ነው። ስለዚህም መልክአ መልክእን ለመረዳት የባለ መልክኡን ታሪክና ትምህርተ ሃይማኖት ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሐላ ዘኢይሔሱ
ዘአንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮንሱ
ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ባሕርየ ከርሡ
አክሊለ ስምከ እንዘ ይትቀጸል በርእሱ
አህጉረ ጸር ወረሰ ኢያሱ /መልክአ ኢየሱስ፣ አርኬ 1/

ይህን አርኬ ለመረዳት የመስፍን እስራኤል ኢያሱን ታሪክ፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትውልድና ምሥጢረ ሥጋዌ ማወቅ ያሻል። የኢየሱስና የኢያሱና የስም አንድነት ማወቅም አስፈላጊ ነው። ኢያሱ የተስፋይቱን ምድር የመውረሱ ታሪክና የጌታችንን ከዳዊት ዘር መወለድንም ማወቅ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ እንደየወቅቱ መጠን የዚህን አርኬ ትርጓሜ እያሰፋና ጥልቀት እየሰጠ መቀጠል ይችላል።

## 2. አስነኛኘት /Prosody/

አስነኛኘት የተባለው የግጥሙን ውጫዊ ገጽታ የሚያሳዩትን ቤት ምትና አርኬን ነው።

### 2.1. ቤት

በመልክአ መልክእ የስንኞቹ የመጨረሻ ቤት መምቻ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ሆሄ ነው። መልክአ መልክእ ሁልጊዜም በአንድ ዓይነት ሆሄ ቤት የሚመቱ ባለ አምስት ስንኝ አርኬዎች ያሏቸው ናቸው።

**ሰላም ለአዕይንቲከ ከመ ምሉዕ ምዕቃለ ማይ**
**እለ ይትረአይ ወትረ በመንበረ መጽሔት ርሱይ /ያጌጠ/**
**ኢየሱስ ክርስቶስ መስተሥርየ ኩሉ ጌጋይ**
**ንዝኃኒ እግዚኦ በአዛብከ ሡናይ**
**ወአጻዕድወኒ እም በረድ ጽሩይ /መልክአ ኢየሱስ፣ አርኬ 6/**
**ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አርኬ ውስጥ ያሉት 5 ስንኞች ቤት የሚመቱት «ይ» በተባለው ሆኖ ነው።**
**የዚህ ቤት መምታት ፋይዳ ስንኞቹ በሚዜሙበት ጊዜ የዜማው አካሄድ እንዲጠበቅ ያደርጋሉ።**

## 2.2. ምት /ቀለም/

ዓለማየሁ ሞገስ /1969/ የግእዝ ሥነ ግጥምን አስነኛኘት ሲያብራሩ የግእዝን ሥነ ግጥም ዜማ የሚወስኑት የሚቆጠሩ ድምፆች /ሆሄያት/ እና የአነባብ ሥርዓት /ተነሽ፣ ወዳቂ፣ ሰያፍ/ ናቸው። እንደ አቶ ዓለማየሁ ሞገስ ጥናት በአንድ አርኬ ውስጥ የሚገኙ ስንኞች የተለያዩ መጠን /የቀለም/ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህም በአንድ አርኬ ወስጥ ያሉ ስንኞች የቀለም መጠናቸው የተለያየ ነው። የሚከተሉት አራት አርኬዎች ቀለም እንደሚያሳየው መልክአ መልክእ አንድ ዓይነት የቀለም መጠን የላቸውም። ከዚህም ሌላ የመጀመሪያው አርኬ ስንኞች ቀለም ከተከታዩ አርኬ ስንኞች እኩል ሆነው የሚጣመዱ አይደለም። ይህም አሰልቺነትን ያስወግዳል።

**/መልክአ ኢየሱስ፣ አርኬ 4/**
**በመልክአ መልክእ አንድ ዓይነት የማይቀያየር ወጥ ዘ የሌለው በባለ አምስት ስንኝ አርኬ ውስጥ አንድ ዓይነት ወጥ ምት ባለመኖሩ ነው። በአጠቃላይ መልክእ ቁርጥ ያለ የምት ቀመር የሌለው ሲሆን ዜማዊ ነው።**

## 2.3. አርኬ

ሰላም ለመክእኪ ዘተሠርገወ አሚረ 16. ... ሀ
ዘያበር ወትረ 7... ለ
ፍቅርትየ አንቲ እንተ ታበድሪ ፍቅረ 14... ለ
አርእይኒ ገጸ ዚአኪ ማርያም ምዕረ 16....ሀ
ዘኢይሰምዕ ካልዕ እንግረኪ ነገረ 14...ለ
/መልአክአ ማርያም፣ አርኬ 51/
ሰላም ለገጽከ እም ሥነ ኦርያሬስ ስቡሕ 15...ሀ
ወፍሡሕ ከመ ወርኅ ዘአሜ ገሃህ 12...ለ
ኢየሱስ ክርስቶስ ታቦተ ሕይወቱ ለኖኅ 12...ለ
ኅብአኒ እግዚኦ በውሳጤከ ስፉሕ 12...ለ

ማየ ኩነኔ አመ ዘንመ አይኅ /ጥፋት፣ የጥፋት ውኃ/ 12 ...ለ
መልክአ መልክእ በአርኬዎች የተከፋፈሉ ግጥሞች ናቸው። እያንዳንዱ አርኬ አምስት አምስት ስንኞች አሉት። ባለ አምስት ስንኝ አርኬዎች በሌሎችም የግእዝ የግጥም ዓይነቶች ውስጥ የተለመደ ነው። ባለአምስት ስንኝ አርኬ ከሚጠቀሙት ውስጥ የስንክሳር አርኬዎች፣ ቅኔ፣ ሰዓታት፣ ማኅሌተ ጽጌና ሰቆቃወ ድንግል አንዳንድ ጊዜ ባለስድስት ስንኝ አርኬም ይጠቀማል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት አርኬዎች በሙሉ ይህንን የሚያስረዱ ናቸው። ለምሳሌ ግን የሚከተለውን አርኬ እንመልከት።

**ሰላም ለፍልሰተ ሥጋከ ለዘርዐ ያዕቆብ ዘተከስተ /1/**
**ወሊቀ ካህናት ገብርኤል ዘሐዘልኮ መዓልተ /2/**
**ዜና ማርቆስ ያዕቆብ ፈውሶተ ድውይ ሐውልተ /3/**
**አቅሞ በቅድሜየ እንዘ ታስተበቁዕ አንተ /4/**
**ኅበ አምላክከ ሰማያዊ ለቤዛ ዘሞተ። /5/**
**/መልክአ ዜና ማርቆስ፤ አርኬ 48/**

በብዙ መልክአ መልክእ አርኬዎች የመጀመሪያ ስንኝ ላይ የሚገኘው መነሻ ቃል ሰላም ነው። ታትመው ከሚገኙት 50 መልክአ መልክእ ውስጥ የአርባ አንዱ መልክአ መልክእ አርኬዎች የመነሻ ቃል ሰላም ነው። ተማኅፀንኩ የሁለት መልክአ መልክእ «ኦ» «ንኢ» እና «ነአ» የአንዳንድ መልክአ መልክእ

አርኬዎች መነሻ ቃላት ሲሆኑ የሦስት መልክአ መልክእ አርኬዎች መነሻ ቃል የላቸውም። በአጠቃላይ ሲታይ ሰላም የመልክአ መልክእ አርኬዎች መነሻ ቃል ነው።

በመልክአ መልክእ አርኬዎች ውስጥ ከመነሻ ቃሉ ቀጥሎ የሚመሰገነው የባለ መልክአ የአካል ስም ወይም ሌላ ነገር ይከተላል። ከ50 መልክአ መልክእ ውስጥ አርባ አንዱ የባለመልክኡን የሰውነት ክፍሎች እየዘረዘሩ የሚያመሰግኑ ናቸው። አራቱ የየባለመልክኡን ተግባራትና አንዳንድ ሁነቶችን፣ አራቱ ደግሞ ምንም የተለየ የሚዘረዝሩት ነገር የለም። የቀሩት ሁለቱ መልክአ መልክእ ግን የተጻፉት ለጸሎት መጻሕፍት ነው። ለውዳሴ ማርያምና ለአንቀጸ ብርሃን የነዚህ ሁለት መልክአ መልክእ አርኬዎች መነሻ ቃል የጸሎት መጻሕፍት አንቀጾች መነሻ ቃል ነው። ለምሳሌ «የመልክአ አንቀጸ ብርሃን» የመጀመሪያዎቹ ሦስት አርኬዎችና የአንቀጸ ብርሃን የመጀመሪያዎቹ ሦስት አናቅጽ መነሻ ቃላት ቅድስት፣ አሠርቱ እና ቀዲሙ ናቸው።

የባለመልክኡን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች የማያዘረዝሩና የማያመሰግኑ ነገር ግን የባለ መልክኡን መለያ ሁነት የሚናገሩ አንዳንድ መልክአ መልክእ አሉ። ለምሳሌ በብራና ላይ ተጽፎ በጀመዶ ማርያም ገደም የተገኘ መልክአ ልደታ ከየአርኬዎች ሁሉ በመነሻ ሐረግነት የተጠቀመው «ሰላም ለልደትኪ ...» የሚለውን ነው። የታተመው «መልክአ ልደታ ለማርያም» የድንግል ማርያምን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች እየዘረዘረ የሚያመሰግን ቢሆንም ልደቷን ካሉት 31 አርኬዎች ውስጥ በሃያ ዘጠኙ ይጠቅሰዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ «በመልክአ ፍልሰታ ለማርያም» ውስጥ የትንሣኤዋንና የሥጋዋን ዕርገት ከሚያመሰግኑት መጨረሻዎቹ ሁለት አርኬዎች በስተቀር የሁሉም አርኬዎች መነሻ ሐረግ «ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ» ነው።

መልክእ የተደረሰለት ግዑዝ ነገር ወይም የተቀደሱ ዕለታት ሰዋዊ ባሕርይ ተሰጥቷቸው ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎች እንዳላቸው ተደርገዋል። ለምሳሌ ሰንበትን ብንወስድ በመልክአ ሰንበት ውስጥ የሰውነት ክፍሎች ተዘርዝረው ሲመሰገኑ እናያለን።

**ሰላም ለከናፍርኪ ዘነበበ በሁባሬ**
**እንበለ ድማሬ**
**ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት ሙዳየ ምጽዋት ዘቤተ ጎሬ**
**እስዕለኪ እግዝእትየ እስመ አቅረብኩ ዝማሬ**
**ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሊተ ጸግወኒ ፍሬ /መልክአ ሰንበት፣ አርኬ 10/**

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አርኬ የተመሰገነው የሰውነት ክፍል ከንፈር ነው፤ ነገር ግን ሰዋዊ ባሕርይ ካልተሰጠው በቀር ዕለት ከንፈር የለውም። ግዑዝና ረቂቅ ሐሳቦችን ሰዋዊ ባሕርይ ሰጥቶ ማመስገን እንደ አንድ ባሕርይ የሚቆጠር ነው።

መልክአ መልክእ በአንደኛ መደብ የተጻፉ ሲሆን ባለመልክአ መልክኡ ደግሞ በሁለተኛ መደብ የሚጠሩበት ግጥም ነው። በተጨማሪም ደራሲው ወይም መልክእን ደጋሚው በአንደኛ መደብ ባለመልክእ ደግሞ በሁለተኛ መደብ ሆነው በቀጥታ እንደሚነጋገሩ ሆኖ በመጻፍ የልመናና ምልጃ ማቅረቢያም ነው።

በየመልክአ መልክኡ ውስጥ በቋሚነት የሚገኘው እኔ የሚለው ተውላጠ ስም በደራሲው ወይም በደጋሚውና በባለመልክኡ መሐል መንፈሳዊ መቀራረብን መፍጠሪያ መንገድ ነው። እኔ የሚለው ተውላጠ ስም ጸሎተኛውን ወይም ልመና አቅራቢውን በመልክኡ ደራሲ ቦታ ራሱን እንዲያስቀምጥ አድርጎ በእሱ /እሷ/ እና በባለመልክኡ መካከል ግላዊና ቀጥተኛ ግንኙነት ፈጥሮ ለባለመልክኡ ልመናውን እንዲያቀርብና ኃጢ አቱን እንዲናገር አስችሏል። ይህ ራስን በመልክአ ደራሲ ቦታ መተካት አንድ ቦታ ችግር ሲገጥመው እናያለን።

# ተዝካርና ፍትሐት

ቤተ ክርስቲያን ስለ ሙታን የምትፈጽመው ሥርዓት ስለ ወዲያኛው ዓለም ያላትን እምነቷን፣ ስለ ሰው ሕይወት ያላትን ትምህርቷን የሚገልጽ ነው።

***ክፍል አንድ***

ቤተ ክርስቲያን የዚህን ዓለም ተጋድሎ ጨርሰው በሚያርፉበትና ወደ ቀጣዩ ዓለም በሚጓዙበት ጊዜ ለልጆቿ ምእመናን የምትፈጽማቸው ሥርዓቶች አሏት:: እነዚህ ልጆቿ በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ከእግዚአብሔር ሕግ እስካልተለዩ ድረስ ልጅነታቸውን የሚፍቀው የለም:: ስለሆነም በምድር በአካለ ሥጋ ለሚኖሩ ልጆቿ የሚገባቸውን እንደምትፈጽም ሁሉ በአጸደ ነፍስ ስላሉትም የሚገባቸውን ታደርጋለች::

ቤተ ክርስቲያን ስለ ሙታን የምትፈጽመው ሥርዓት ስለ ወዲያኛው ዓለም ያላትን እምነቷን፣ ስለ ሰው ሕይወት ያላትን ትምህርቷን የሚገልጽ ነው::

## ሀ. ስለ ወዲያኛው ዓለም ያላት እምነት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኀዘንና በልቅሶ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈላቸው መልእክቱ «መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ ሐሳባቸው ምድራዊ ነው» በማለት እንደተናገራቸው ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ነገር መጨረሻ ምድር ነው ብላ አታምንም:: ነገር ግን «እኛስ ሀገራችን በሰማይ ነው» ያለውን ትምህርት ተከትላ ከዚህ የበለጠ ታላቅ ሕይወት በሰማያዊ ማዕረግ በሰማይ መኖሩን ታምናለች ታስተምራለች:: /ፊልጵ.3ኮ18-21/::

«ብዙዎች ከምዕራብና ከምሥራቅ ይመጣሉ፤ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ» በማለት ጌታችን እንዳስተማረን በምዕራብና በምሥራቅ ተሠማርተው ከሕዝብም ከአሕዛብም ወገን ወጥተው ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ የደጋግ አበው ማኅበርተኞች የሚሆኑ ልጆች እንዳሏት ታምናለችኮ ታስተምራለች:: /ማቴ.8ኮ12/::

ቤተ ክርስቲያን ስለ ሙታን የምትፈጽመው ሥርዓት በወዲያኛው ዓለም ያሉ ልጆቿና በዚህ ዓለም ያሉ ምእመናን አንድነት እንዳላቸው ማሳያ ነው:: አባታችን አብርሃምና ባዕለ ጸጋው ነዌኮ በዚህ ምድር በነበረ ጊዜ የሆነውን ሁሉ ጠንቅቆ እንዳወቀ ሁሉ በወዲያኛው ዓለም ያሉት ስለዚህኛው ዓለም ምእመናን ሕይወት እንደሚያውቁ /ሉቃ.16ኮ23/ በዚህ ምድር ያሉትም በወዲያኛው ዓለም ስላሉት ምእመናን እንደሚያስቡ /2ጢሞ.1ኮ18/ በወንጌል የተጻፈውን በምግባር ይገልጣል::

በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን ስለ ሙታን የምትፈጽመው ሥርዓት የሰው የኑሮው መጨረሻ ምድር ያለመሆኑን፣ በዚያኛው ዓለምና በወዲህኛው ዓለም ምእመናን መካከል ያለውን የሃይማኖት አንድነት እንደምታምን መገለጫ ነው::

## ለ. ስለ ሰው ሕይወት ያላት ትምህርት

ምእመናን የቅድስት ሥላሴን ልጅነት ካገኙ /በልዑል እግዚአብሔር ሕግ ጸንተው እስከ ኖሩ የጉባኤ እግዚአብሔር አቅሌሲያ /ቤተ ክርስቲያን/ አባል እስከ ሆኑ በእምነት በምግባር ለመጽናት እስከ ተጋደሉ ድረስ ሰውነታቸው ክቡር፣ ቅዱስ፣ በረከታቸው ለሕዝብ ለሀገር የሚጠቅም፣ መካናቸው ማኅደረ ምሕረት፣ ጸሎታቸው አዳኝ፣ ቃል ኪዳናቸው ጠባቂ መሆኑን ታምናለች:: /ጥበብ 4ኮ15-16፣ 2ዜና.21ኮ12-14፣ 1ቆሮ.13ኮ12፣ማቴ.10ኮ48/::

ይህ ደግሞ በመጽሐፍ «ሥራቸው ይከተላቸዋል» እንደተባለ በዚህኛው ዓለም ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም:: በወዲያኛውም ዓለም አብሯቸው ይኖራል:: /ራእይ 14ኮ13:: በመሆኑም በሃይማኖት ኖረው የሚሞቱ አበው ካህናትና ምእመናን:-አጽማቸው ይከበራል ከረሃብ ያዳናቸውን፣ ኀዳጊ በቀል ሆኖ ይቅር ያላቸውን፣ ለአብነትም በግብፅ ምድር ርስት ያስገኘላቸውን ታላቅ አባት የዮሴፍን አጽም አሥራኤል ከግብጽ ሲወጡ አፍልሰው ወስደውታል:: /ዘጸ.13ኮ19/:: ምክንያቱም የደጋግ አበው አጽም የበረከት ምንጭ ነውና:: በሌላም በኩል በዘመነ ዕጸባ፣ በዘመነ ስደት ከዐቅም በላይ ካልሆነ በቀር የእግዚአብሔር ሰዎች አጽም በአልባሌ ቦታ አይቀመጥምና ነው::

የኤልሳዕ አጽም ሙት እንዳስነሣው በሃይማኖት በምግባር ሳሉ የሞቱ፣ ትንሣኤ ልቡና የሚያስፈልጋቸውን በመካናቸው ሲገኙ ያስነሣሉና /2ነገ.13ኮ20/ የአባቶቻችን አጽም በክብር እንዲያርፍ ይደረጋል:: በዘመነ ተጋድሏቸው ከሰው ተሠውረው ቢያርፉ ወይም ደግሞ በዋሻ በፍርክታ ቢያንቀላፉ እንኳን ጊዜው ሲደርስ በራእይ በተአምራት ተገልጠው ፍልሰተ አጽም ይደረግላቸዋል፤ /ለዚህም የአቡነ ተክለ ሃይማኖትንና የአቡነ ዜና ማርቆስን ታሪክ መመልከቱ በቂ ማስረጃ ነው/::

### ሥጋቸው በክብር ይገነዛል

ምእመናን ሲሞቱ ተጋድሎ የፈጸሙበት አካል ክቡር ቅዱስ ነውና ሰውነታቸው ይታጠባል፡፡ /የሐዋ.9ኮ37/፣ ስመው ይሰናበቱታል /ሥርዓተ ስዒም ይፈጸምላቸዋል፤ ዘፍ.50 ኮ1/፡፡ በሽቱ ወይም መዓዛው መልካም በሆነ ነገር ያሻሿቸዋል፡፡ /ዘፍ.50 ኮ1/፡፡

## በክቡር ቦታ ይቀብሯቸዋል

የምእመናን ሥጋ አይቃጠልም ወይም የትም አይጣልም፡፡ በሥርዓት ሊቀበር ይገባዋል፡፡ /የሐዋ.8ኮ2/፡፡ መቃብራቸውም በቤተ መቅደስ ዙሪያ መሆን ይገባዋል፡፡ /ፍ.ነ.ፍ.መ.22 ቁ.786/፡፡

## መቃብራቸው ሊከበር ይገባዋል

የምእመናን ሥጋ ያረፈበት ቦታ አልባሌ አይደለም፡፡ በሥርዓት ሊከበር ሊጠበቅ ይገባዋል፡፡ /ፍ.ነገሥት ፍ.መ.22 ቁ.798/፡፡
ቤተ ክርስቲያን ለሰው የመጨረሻውን ደረጃ ክብር የምትሰጥ፣ በሕይወተ ሥጋም በሕይወተ ነፍስም እናትነቷ የማይታጠፍ ናት፡፡ እንተ በምድር ሥረዊሃ /ሥሮቿ በምድር/ ወበሰማይ አዕጹቂሃ /ጫፎቿ በሰማይ/ ናትና ሰማያውያንን ከምድራውያን ታገናለች፡፡

# ፍትሐት

ፍትሐት ማለት «ፈትሐ» ካለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው፡፡ ትርጒሙም መፍታት፣ መልቀቅ ማለት ነው፡፡ በሃይማኖታዊ ትርጒሙ ደግሞ ከኃጢአት እስራት መፍታት ነጻ ማድረግ ማለት ነው፡፡ «በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ሲል የፈታችሁት የሚለው ቃል «ከኃጢአት ይቅር ያላችሁትኮ ያስተሰረያችሁለት» ማለቱ ነው፡፡ /ማቴ.16ኮ19/፡፡
ለሥርዓተ ፍትሐት አራት መሠረታዊ ነጥቦች ይጠቀሳሉ

1. እስከ መጨረሻው የፍርድ ቀን ድረስ ጻድቃንም ኃጥአንም ዐርፈው ተጠብቀው የሚቆዩበት ቦታ አለ ብሎ ማመን
በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የመጨሻዎቹ ርስቶች /ለጻድቃን መንግሥተ ሰማያት፣ ለኃጥአን ገሃነመ እሳት/ እስከሚከፈቱና የመጨረሻው ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ኃጥአን በሲኦል ጻድቃን በገነት ይቆያሉ፡፡ ፈያታዊ ዘየማን «ዛሬ በገነት ከኔ ጋር ትሆናለህ» መባሉ /ሉቃ.23ኮ40/፡፡ ነዌም በሲኦል እንደነበር መገለጡ /ሉቃ.16ኮ23/ ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «እግዚአብሔር ኃጢአት የሠሩትን መላእክት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የፍርድን ቀን እንዲጠባበቁ ወደ ሲኦል ጣላቸው እንጂ አልራራላቸውም» /2ጴጥ.2ኮ4/፡፡ በማለት የመጨረሻ የፍርድ መጠባበቂያ ቦታ መኖሩን ገልጧል፡፡

ታዖሎጐስ ዮሐንስም በራእዩ «አምስተኛው ማኅተም በተፈታ ጊዜ ... ለእያንዳንዳቸው ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፡፡ እንደ እነርሱ የተገደሉ፤ እነርሱ አገልጋዮች የሆኑ የጓደኞቻቸውና የወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪሞላ ጥቂት ጊዜ ዐርፈው እንዲቆዩ ተነገራቸው» በማለት ጻድቃን የመጨረሻውን ፍርድ የሚጠባበቁበት ማረፊያ መኖሩን ተናግሯል፡፡ /ራእይ.6ኮ9-11/፡፡

2. ነፍስና ሥጋ አብረው በመሆን ለፈጸሙት በጐም ሆነ ክፉ ተግባር ዋጋቸውን ወይም ፍዳቸውን አብረው ይቀበላሉ ብሎ ማመን ነፍስና ሥጋ በዚህ ዓለም የኖሩት ሥራ የሠሩት አብረው ተዋሕደው «ሰው» ተብለው ነው፡፡ በመሆኑም በመጨረሻው ቀን ተዋሕደው ተነሥተው ዋጋቸውን ወይም ፍዳቸውን በጋራ ማግኘት አለባቸው፡፡

3. ከሞት በኋላ የሚደረግ ጸሎት ድኅነትን ያስገኛል ብሎ በማመን
ጌታችን «በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብን ቃል የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ኃጢአቱ አይሰረይለትም» በማለት ያስተማረው ትምህርት /ማቴ.12ኮ32/ በሚመጣው ዓለም ይቅር የሚባልና የማይባል ኃጢአት መኖሩን ያስረዳናል፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስም በመልእክቱ «ማንም ወንድሙን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፡፡ ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል፡፡ ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፡፡ ስለዚህ እንዲጠይቅ አልልም፡፡ ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው፡፡ ሞትም የማይገባው ኃጢአት አለ፡፡» /1ዮሐ.5ኮ16/፡፡ በማለት እንዳስተማረን ሞት የሚገባው ሊለመንለት የማይገባ፣ ሞት የማይገባው ሊለመንለት የሚገባ ኃጢአት መኖሩን ተንትኗል፡፡ እዚህ ላይ ሞት ማለት ዘላለማዊ ሞት ነው፡፡ ምክንያቱም በወንጌል ትምህርት በቀኖና እንጂ በሞት ፍርድ መቅጣት የክርስቲያን ሕግ አያዝምና፡፡

በመሆኑም ዘለዓለማዊ ሞት የሚገባውና በምልጃ በጸሎት የጐደለው ተሞልቶለት ሞት የማይገባው ኃጢአት ስላለ የመጨረሻው የሞት ፍርድ ከመፈረዱ በፊት የሚጸለይ ጸሎት ሞት ለማይገባው እስከሆነ ድረስ ዋጋ አለው፡፡

4. ቀደምት አበው የፈጸሙት ዋጋ ያለው ምግባር ነው ብሎ በማመን
ይሁዳ መቃቢስ በጦርነት ለሞቱ ወታደሮች የኃጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት ይደረግላቸው ዘንድ 2000 ድራህማ ወደ ኢየሩሳሌም ልኰ ነበር፡፡ /2መቃቢ.12ኮ43/፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በሞት ተለይቶ ለነበረው ለሄኔስፎሩ «በዚያ ቀን ይስጠው» በማለት ጸልዮለታል፡፡ /2ጢሞ.1ኮ18/፡፡ ለሌሎቹ ሰላምታ ሲያቀርብ ለእርሱ ይኸን መጸለዩ በዚያ ጊዜ በአካለ ሥጋ እንዳልነበር ያሳያል፡፡

በመጽሐፈ ዲድስቅልያም «በጌታ አማኞች የነበሩት ወንድሞቻችሁ ሰማዕታትም ሆኑ ሌሎች ክርስቲያኖች በሚያርፉበት ጊዜ ያለ መሰልቸት በቤተ ክርስቲያን ተሰብስባችሁ ዘምሩላቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን የቅዳሴ ጸሎት አድርጉ፤» ተብሎ ተጽፏል፡፡ /ዲድ. 34/፡፡ ቅዱስ ዲዮናስዮስ «ከሰው ልጅ ደካማነት የተነሣ ሰው ለሚፈጽማቸው አንዳንድ በደሎች በካህኑ ጸሎት አማካኝነት ለሞተው ሰው ይቅርታ ተደርጐለት ወደ ብርሃንና ወደ ሕይወት ቦታ ማለት ወደ አብርሃም ወደ ይስሐቅ ወደ ያዕቆብ ዕቅፍ ይወሰዳል» ብሏል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም «አንድ ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ ቢሞት የምንችለውን ያህል ልንረዳው ይገባል፡፡ የምንረዳውም በልቅሶና በኀዘን ሳይሆን በጸሎት፣ በምጽዋትና በቁርባን ነው፡፡ የዓለምን ኃጢአት ወደ ተሸከመው የእግዚአብሔር በግ፤ ስለ ሙታን የምንጸልየው እነርሱ መጽናናትንና ዕረፍትን እንዲያገኙ ነው እንጂ በከንቱ አይደለም፡፡ ጻድቁ ኢዮብ ስለ ልጆቹ ያቀርብ የነበረው ቁርባን ጠቀሜታ ከነበረው ስለሙታን የምናቀርበው ቁርባን ምንኛ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረው» ብሏል፡፡ /ዮ፤አ.ወ፣ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 41ኛ ስብከት/፡፡

## ክፍል ሁለት

### የጸሎተ ፍትሐት ጥቅም

1. **የአንድነት መግለጫ፡-** ጸሎተ ፍትሐት በዐጸደ ሥጋና በዐጸደ ነፍስ በሚኖሩ ክርስቲያኖች መካከል ያለውን የእምነት አንድነት ይገልጣል፡፡ ነቢዩ ሄኖክ «ሕያዋን ለሙታን ሙታን ለሕያዋን ይጸልያሉ» /12ኮ34/ በማለት እንደተናገረው በዐጸደ ነፍስ የሚገኙ ሙታን በዐጸደ ሥጋ ለሚኖሩት እንደሚጸልዩ ሁሉ በዐጸደ ሥጋ ያሉትም በሞት ለተለዩት ይጸልዩላቸዋል፡፡ ይህም የክርስቲያኖችን አንድነት ገላጭ ነው፡፡

2. **ለኃጢአት ማስተስረያ፡-** «አንድ ሰው ባለማወቅ ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ቢተላለፍ በደለኛ ነው፡፡»/ ዘሌ.5ኮ17/ በማለት ልዑል እግዚአብሔር ለሙሴ እንደነገረው ሰው ባለማወቁ በሚሠራው ኃጢአት ከሚመጣው ፍርድ ነጻ መሆን አይችልም፡፡ ሰው በማወቅ፣ ባለማወቅ ኃጢአት መሥራቱ ሳይሰማው ሊሳሳት ይችላል፡፡ የሚያስታውሰውን ንስሐ ገብቶ ተናዝዞ ቀኖና ይወስድበታል፡፡ ለማያውቀው ለረሳው ደግሞ ጸሎት ይጸልይለታል፡፡

ፍትሐትም ጸሎት እንደ መሆኑ ሚቹ ሳይናዘዝ ለሞተው ኃጢአት ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ይቀርባል፡፡ «ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን፤ እውነትም በኛ ውስጥ የለም፡፡» /1ዮሐ.1ኮ8/ በማለት ወንጌላዊው ዮሐንስ እንዳስተማረው ኃጢአት የለብኝምና ፍትሐት አያስፈልገኝም ማለት የሚችል ሰው የለም፡፡ «አንድ ሰው ኃጢአ ተኛ እንደሆነ ቢሞት የምንችለውን ያህል ልንረዳው ይገባል፡፡ የምንረዳውም በልቅሶና በኃዘን ሳይሆን በጸሎት፣ በምጽዋትና በቁርባን ነው፡፡» በማለት ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተናገረ፡፡

# ተዝካር

«ተዝካር» የሚለው ቃል «ዘከረኮ አሰበ፣ ስም ጠራ» ካለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን መታሰቢያ ማለት ነው፡፡ መታሰቢያውም የሚደረገው ለሙታን ሲሆን የሚቀርበውም በጸሎት፣ በመሥዋዕት፣ በመብራት፣ በማዕጠንትና በምጽዋት ነው፡፡ /ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንምኮ ገጽ 49/፡፡ ተዝካርን ማውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትና አበዋዊ ሥርዓት ነው፡፡

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ

ነቢዩና ጥበበኛው ሲራክ «ልጄ ለሞተ ሰው አልቅስለት፤ እዘንለት፤ እንደ አገሩም ተዝካር አውጣለት» ሲራክ 38ኮ16፣ «የሞተ ሰውስ ዐረፈኮ ነገር ግን ነፍሱ ታርፍ ዘንድ ተዝካር አውጣለት ከዚህ በኋላ ልቅሶህን ተው» በማለት እንደሚያስተምረው በሃይማኖት ኖረው ለሞቱ ወገኖች ተዝካር ማውጣት ተገቢ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው» በማለት ተናግሯል፡፡ ምሳ.10 ከ7፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ቤት ኖረው ያረፉ ወገኖች እግዚአብሔርን አገልግለዋልና የእነርሱን ተዝካር ማውጣት ለአውጭው በረከት እንደሚያስገኝ ነው፡፡

## አበዋዊ ሥርዓት

የቤተ ክርስቲያን አባቶች የሞቱ ክርስቲያኖችን ተዝካር ማውጣት ዋጋ እንዳለው ደንግገዋል፡፡ «ስለ ሞቱ ሰዎች ነፍሳት ከገንዘባቸው ለድኾችና ጦም አዳሪዎች ይመጸውቱላቸው፡፡» /መጽሐፈ ሲኖዶስ/፡፡ «በክርስቶስ አምነው ስለሞቱ ወንድሞቻችሁ ክርስቲያኖችና ሰማዕታት በቤተ ክርስቲያን ያለ ሐኬት ተሰብሰቡ፤ በቤተ ክርስቲያን መሥዋዕት ሠውላቸው፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ መቃብር ስትወስዷቸውም መዝሙረ ዳዊት ድገሙላቸው፡፡» /ዲድ.34/፡፡

«ስለ ሞቱ ሰዎች በሦስተኛው ቀን፣ በሰባተኛውም ቀን ቁርባን ሊያስቀርቡ ይገባል፤ በስድስት ወርና በዓመቱም መጨረሻ ይልቁንም ቢቻላቸው ከተቀበረበት ቀን ጀምሮ እስከ 40 ቀን ቁርባን ያስቀርቡ ለነዳያንም ይስጡ፡፡» /ፍ.ነ.ፍ.መ 22ከ790-794/፡፡

## ተዝካር ለምን ይወጣል?

1. ***ዕረፍተ ነፍስን ለማግኘት*፡-** ስለ ፍትሐት ስንጽፍ እንደገለጥነው በንስሐ ቀኖና ላልተሰረየ ኃጢአት ቀሪዎቹ ምእመናን ፍትሐት /ጸሎት/ ያደርጋሉ፣ ተዝካር /መታሰቢያ/ ያወጣሉ፡፡ በዚህም የሟች ነፍስ ዕረፍተ ነፍስን ታገኛለች ሲራክ. 38ከ23፡፡ ይህም ዕረፍት ነፍስ ምንም ያህል ዕዳ ቢኖርባት ልዑል እግዚአብሔር የወገኖቿን ልመና ሰምቶ ይቅር በማለቱ የምታገኘው ዕረፍት ነው፡፡

2. ***ለቋሚዎቹ ዋጋ ለማግኘት*፡-** ሟቹ እውነተኛ ክርስቲያን፣ በምግባር በሃይማኖት የኖረ የእግዚአብሔር ሰው ከሆነ የርሱን መታሰቢያ ማውጣቱ በዳዊት ቃል እንደተገለጠው በረከት ያስገኛል፡፡

## ፍትሐትና ተዝካር ለማን?

ምንም እንኳን የሚጸለይ ጸሎት፣ የሚበራ መብራት፣ የሚሠዋ መሥዋዕት ተስፋና ሃይማኖት ስላለበት ዋጋ ባያጣም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትምህርት ፍትሐትና ተዝካር የሚገባቸውና የማይገባቸው አሉ፡፡

ፍትሐትና ተዝካር የሚገባው በሃይማኖት በምግባር ጸንተው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ሲሳተፉ ኖረው ለሞቱ ሰዎች መሆኑን መጽሐፈ ሲኖዶስ ደንግጓል፡፡ በዲድስቅልያ ላይም «በክርስቶስ አምነው ስለ ሞቱ ወንድሞቻችሁና ሰማዕታት» በማለት ፍትሐትና ተዝካር ለማን እንደሚገባ በግልጥ አስቀምጧል፡፡ /ቁ.34/፡፡ በመሆኑም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ለኖረ፣ ከሃይማኖቱ ላልወጣ፣ በምግባሩ ለመቅናት ለተጋ፣ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ለኖረ ፍትሐትና ተዝካር ቢያወጡለት ለርሱም ለአውጭውም ዋጋ ይኖረዋል፡፡

ከዚህ ውጭ ግን ለመናፍቅና ለከሃዲ ከሕገ ክርስትና ወጥቶ በዓመፅና በዕብሪት ለኖረ ሰው ፍትሐትና ተዝካር ማውጣቱ ምንም ዋጋ እንደሌለው በዓመፀኛው ባዕለ ጸጋ በነዌ ታሪክ እንረዳለን፡፡ ነዌ በሕይወቱ እያለ ዋጋ ያለው ሥራ ባለመሥራቱ ከሞተ በኋላ ላቀረበው የምሕረት ጥያቄ «አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፡፡ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናልኮ አንተም ትሰቃያለህ» የሚል መልስ ነው ያገኘው፡፡ /ሉቃ.16ከ25/፡፡

ሐዋርያትም በሲኖዶሳቸው «የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚክዱ ሰዎች በዓለም ያለውን ገንዘብ ሁሉ ቢመጸውቱላቸው ምንም አይጠቅማቸውም» በማለት ተናግረዋል፡፡
በሌላ በኩል በራሱ እጅ ለሞተ ሰው ፍትሐትና ተዝካር አይደረግለትም፡፡ እርሱ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ለራሱ ለመውሰድ ፈልጓልና፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣ አንድ ጥያቄ አለ፡፡ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ፍትሐትና ተዝካር የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ለይቶ ካስቀመጠ ለምን ለሁሉም ምእመን /ሰው/ ፍትሐት ሲደረግ ይታያል? ይህ ጉዳይ ንስሐ የገባውንና ያልገባውን በምግባር የኖረውንና ያለኖረውን በትክክል ለይቶ ማወቅ በሚያስቸግርበት ጊዜ ፍርዱን ለእግዚአብሔር በመተው የሰውን ድርሻ ለመውጣት የሚደረግ እንጂ ሥርዓቱን በመጣስ የሚከናወን አይደለም፡፡

## ተዝካር በምን?

ለመሆኑ ተዝካር ለማውጣት የግድ ላቅ ያለ ድግስ መደገስ ግዴታ ነውን? መልሱ አንድ ብቻ ነው፤ አይደለም፡፡ ተዝካር የሚወጣው በምን በምን እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት «በጸሎት፣ በመሥዋዕት፣ በመብራት፣ በማዕጠንትና በምጽዋት» በማለት ተንትኖታል፡፡ በጸሎት ፍትሐቱ፣ ዳዊት መድገሙ፤ በመዋዕት የቅዳሴ መሥዋዕቱ፤ በመብራት በጧፍ፤ በማዕጠንት በዕጣን መሥዋዕት፣ በምጽዋት በገንዘብ፣ በልብስ፣ በእህል ውኃ ወዘተ በሚሰጥ ልገሣ ነው፡፡

በመሆኑም ተዝካር ወጣ ማለት የሟች ስም በጸሎት እንዲነሣ፣ ቅዳሴ እንዲቀደስ፣ ቁርባን እንዲቆረብ ማድረግ፤ ከሀብቱ ከፍሎ ለድኾችና ለጦም አዳሪዎች መመጽወት ማለት እንጂ ድግስ ደግሶ ዘመድ ጐረቤቱን ጠርቶ መብላት መጠጣትና ብድራትን መመላለስ ማለት አይደለም፡፡ ይህ ባሕል እንጂ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አይደለም፡፡ ከገንዘቡም መስጠት ያለበት «ለድኾችና ጦም አዳሪዎች» መሆኑን መጽሐፈ ሲኖዶስ ይገልጣል፡፡

## ካህናትስ?

ካህናት መሥዋዕት የሚሠው፣ መብራት የሚያበሩ ጸሎት የሚያደርሱ በመሆናቸው «የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሠር» ነውና ቁመት አድረውኮ ቅዳሴ ውለው እህል ውኃ መቅመሳቸው ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ ውጭ ግን ገበሬው በሬውን አርዶ፣ ነጋዴው ካዝናውን አራግፎ፣ ሠራተኛው ተበድሮ ተለቅቶ ከዐቅሙ በላይ የሚደግሰው ድግስ ሆዴ ይሙላ ደርቴ ይቅላ ከማለት ውጭ መንፈሳዊ ዋጋ አይኖረውም፡፡

ምንጭ፡-
ዬ ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም፣ 1991 ዓ.ም
ዬ አሥራት ገ/ማርያም፣ ትምህርተ መለኰት፣ 1991 ዓ.ም
ዬ ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ፣ መርሐ ጽድቅ ባሕለ ሃይማኖት፣ 1988
ሐመር መጽሔት 1995 ዓ.ም

# አሥራት ምንድን ነው? ለምንኮ እንዴትና ለማን ይሰጣል?

## አሥራት ምንድን ነው?

አሥራት ዐሥሮ፤ ዐሠረ፤ አዐሠረ ተዐሠረ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ዐሥር አደረገ፣ ዐሥር ማድረግ፣ ካሥር ተከፈለ፤ ዐሥር ተባለ ማለት ነው፡፡ በዕብራይስጡ ወሱር፣ ዐሣር፣ በዐረብኛው ደግሞ ዐሸረ ይላል፡፡ አሥራት በሰዋስዋዊ ትርጉሙ፤ ዐሥረኛ እጅኮ ክፍል፤ ከአሥር አንድ ቀረጥ፤ ግብር መስጠት፣ መቀበል ወይም መውሰድ ማለት ነው፡፡ /ኪ.ወ.ክ ገጽ 700 -7001/፡፡ በመንፈሳዊ ይዘቱም ክርስቲያኖች ከማንኛውም ገቢያቸው አሥረኛውን እጅ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጡ በትን ሥርዓት ያመለክታል፡፡ /ዘሌዋ.27ኮ30-33፣ ዘዳግ.12ኮ5-18፣ 14ኮ22-29፣ ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ. መንፈሳዊ 18ኮ673-675፣ መጽ.ዲድ.7/፡፡ ምእመናን አሥራታቸውን በከፈሉ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር እነርሱንና ለእነርሱ ያላቸውን ሁሉ ይባርካል፡፡ /ዘዳግ.26ኮ13-15፣ ሚል.3ኮ10/፡፡

በመሠረቱ አሥራት የሚለው ሕጉ ሥርዓቱ በብሉያትም ሆነ በሐዲሳት ቅዱሳት መጻሕፍት ምንጩ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ዘፍ.14ኮ20፣ 28ኮ22፡፡ ሥርዓቱም የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው ብለን አሥራት የሚለውን ሕግ እንዳለ ተቀበልነው እንጂ በዘመነ ወንጌል ብዙ ጊዜ ከአሥር አንድ የሚለው ጐልቶ የሚታየው በአፈጻጸም ላይ በሙዳየ ምጽዋት ነው፡፡ በትሩፋት መልክ ማድረግ ነው፡፡ እንዲያውም የተወሰነውን መስጠት ብቻ ሳይሆን ከተወሰነው በላይ መስጠት ማለት ነው፡፡ ሥርዓቱም የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው ብለን አሥራት የሚለውን ሕግ እንዳለ ተቀበልነው እንጂ በዘመነ ወንጌል ብዙ ጊዜ ከአሥር አንድ የሚለው ጐልቶ የሚታየው በአፈጻጸም ላይ በሙዳየ ምጽዋት ነው፡፡ በትሩፋት መልክ ማድረግ ነው፡፡ እንዲያውም የተወሰነውን መስጠት ብቻ ሳይሆን ከተወሰነው በላይ መስጠት ማለት ነው፡፡

### አሥራት የሚወጣው ከጠቅላላ የደመወዝ መጠን ወይስ ከተጣራ የደመወዝ ክፍያ?

ጉዳዩ የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ ክርስትና ሕገ ርትዕ አይደለም፡፡ ሕገ ትሩፋት ነው፡፡ ከመሠረቱ ይኸንን ማወቅ

ያስፈልጋል። ሕገ ርትዕና ሕገ ትሩፋት የተለያዩ ናቸው። ይህን ጥያቄ ወደ ትሩፋት ሳይሆን ወደ ሕግ ገብቶ ነው የምናየው። ወንጌል ሕገ ርትዕ አይደለችም። ሕገ ትሩፋት ነች። ኦሪት ደግሞ ሕገ ርትዕ ናት። የተወሰነውን ነገር መፈጸም ብቻ። ወንጌል ግን ከተወሰነው በላይ ሁሉ መሥራት ነው። ስለዚህ ሕገ ትሩፋት ነው የምትባለው።

ከአሥር አንድ የኦሪት ነው። የወንጌል ሕግ ደግሞ የተወሰነውን ብቻ ወይም አድርግ የተባለውንም ብቻ ማድረግ ሳይሆን አድርግ ከተባለውም በላይ ማድረግ ነው። እና አሥራት የሚለው ከአሥር አንድ በአጭሩ በኦሪትም ቢሆን ከሚያገኘው ላይ ነው እንጂ ከማያገኘው ላይ አይከፍለውም። አንድ ሰው ከሚያገኘው ላይ እንጂ ከማያገኘው ላይ አሥራት አይጠየቅም። ሰውየው ተቀጥሮ የሚሠራ ደመወዝተኛ ከሆነ ከገቢው ላይ ነው። ከጠቅላላ ደመወዙ ላይ ሳይሆን ከተጣራው ተከፋይ ገቢው ላይ ነው፣ አሥራቱን እንዲያወጣ የታዘዘው። የኦሪቱ ሕግ አንድን ሰው ከማያገኘው ላይ አሥራት ክፈል አይለውም። ከሚያገኘው ገቢ ላይ እንጂ።

**አሥራት የሚሰጠው ለማን ነው?**

አሥራት ለማን እንደሚሰጥ በግልጽ ያልተረዱ ምእመናን በየቦታው የተለያየ ጥያቄ ያነሣሉ። አስተያየትም ይሰጣሉ። አንዳንዶች አሥራት የሚሰጠው ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ የአሥራት ማኅበር አቋቁመው አሥራታቸውን እያሰባሰቡ ያጠራቅሙና በየገጠሩ ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት ጧፍ ዕጣን ያቀርባሉ። የፈረሱትን ይጠግናሉ። የወሰነው ለንስሐ አባት መስጠት አለበት የሚሉም አሉ። ለተቸገሩ ሰዎች መስጠት መርዳትም አሥራትን እንደማውጣት ነው የሚሉም አሉ።

አሥራትን ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ማለት እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉ ካህናት መስጠት ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ከሕዝቡ መካከል ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ በኩሮች ነበሩ። በኩራት የሚባሉ የበኩር ልጅ ሁሉ ቤተ እግዚአብሔርን ማገልገል ግዴታ ስለሆነ ለቤተ እግዚአብሔር ይሰጥ ነበር። ቤተ ሌዋ ለቤተ ክህነት ከተመረጡ በኋላ ግን ቤተ ሌዋ እና ቤተ አሮን ርስት አልባ እንዲሆኑ ተደርጓል። ለምን? ርስታቸው እግዚአብሔር ነው። ርስታቸው ሕዝቡ ነው። በእርሻ ወይም በሌላ ሥራ እንዲተዳደሩ ሳይሆን ከሕዝብ በሚያገኙት አሥራት እንዲተዳደሩ፣ ርስታቸው ጉልታቸው አሥራት እንዲሆን፣ ሥራቸው በቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት እንዲሆን ተብሎ ተወስኗል። ዘኁል.18ቁ8። ስለዚህ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው ነገር ሁሉ ለካህናትም ነው የሚሰጠው። የካህናት ማደሪያ ነው።

ለቤተ እግዝአብሔር የሚሰጠው ለካህንም ስለሆነ ለካህን ለብቻው የሚሰጥ የለም። ለቤተ እግዚአብሔር መስጠትን ለካህን ከመስጠት ነጥሎ ማየት አይቻልም። እንዲህም ሆኖ ግን ካህናቱም ቢሆኑ የአሥራት አሥራት ይከፍላሉ። እንዲያውም ፈሪሳውያን ከቅመማ ቅመም ሳይቀር ይከፍሉ ነበር። ማቴ.23ቁ23። እነሱ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠውን አሥራት ይቀበላሉ። ለቤተ እግዚአብሔር መሥዋዕት የሚሆነውን የሚያስፈልገውን ሁሉ ካወጡ በኋላ የተረፈው የካህናቱ የዕለት ተዕለት መተዳደሪያቸው ይሆናል። ስለዚህ ለቤተ እግዚአብሔር የተሰጠ አሥራት ለካህንም ተሰጠ ማለት ነው።

አሥራት የተሠራው በብሉይ ኪዳን ነው። ለድሀ ተብሎ አይደለም። ለቤተ እግዚአብሔር ተብሎ ነው። የቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን፣ ቤተ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ካህናት ተቸግረው አገልግሎቱ እንዳይጓደል፣ ካህናቱ በሌላ የመተዳደሪያ ሥራ ተሠማርተው አገልግሎቱን እንዳያስተጓጉሉ ወይም እንዳያጓድሉ ለእነሱ ማደሪያ የሚሰጥ እንጂ ለድሀ ተብሎ አይደለም። አሥራት የተፈቀደው መጀመሪያ ሥርዓቱ የወጣው ለቤተ እግዚአብሔር ነው። ለድሀ የሚሰጠው ለቤተ እግዚአብሔር ከሚሰጠው አሥራት የተለየ ነው። ነገር ግን ከዚህ ውጪ ለድሆች የተለየ ነገር አለ። ለምሳሌ በኦሪቱ ድሆች ምርት በሚሰበሰብበት ጊዜ ቃርሚያ እንዲለቅሙ በአጨዳ ጊዜ የወደቀ ነዶ እንዳይነሣ ይደረጋል። በማሳም ሆነ በውድማ ላይ የረገፈ እህል የወደቀ ነዶ የሚተወው ለድሆች ነበር። በብሉይ ኪዳን ጊዜ ዋርሣ መውረስ /የሚች ወንድም ሚስት መውረስ/ ሕግ ስለ ነበረ ችግረኛ ቤተሰብ ላይኖር ይችላል። ለምሳሌ አሁን በሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ድሀ አደጎችንና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን መበለቶች አደራ በማለት አጠንክራ ታሳስባለች። በኦሪቱ ግን በሐዲስ ኪዳን ያለው ዓይነት ችግር የለም። ዋርሣ መውረስ ስላለ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች የባሎቻቸው ወንድም ስለሚያገቧቸው እና ልጆቻቸውን ስለሚያሳድጉላቸውና በሐዲስ ኪዳን የሚታየው ዓይነት ችግር በዚያን ጊዜ አልነበረም። በሐዲስ ኪዳን ግን ዋርሣ መውረስ ስለሌለ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶችና ድሀ አደግ ልጆችን አደራ የሚባለው ለዚህ ነው። ስለዚህ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው አሥራት ለድሆች የሚሰጠው ደግሞ ምጽዋት ይባላል።
ከአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ውጪ ለሌሎች የተቸገሩ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት መስጠት አሥራት እንደማውጣት አይቆጠርም። ለሌላ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ነገር መባዕ ነው የሚባለው። አንድ ምእመን ለፈለገው ቤተ ክርስቲያን መባዕ መስጠት ይችላል።

ምእመናን ከሚያወጡት አሥራት የተወሰነው የንስሐ አባት ድርሻ ነው በማለት ለንስሐ አባታቸው የሚሰጡ አለ የሚል ሐሳብ ተነሥቷል፡፡ እንግዲህ ደመወዝ በሌለበት ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱ የነፍስ ልጅ /የንስሐ ልጅ/ ለንስሐ አባቱ ይሰጣል፡፡ በደመወዝ የሚተዳደሩ ካህናት ከሆኑ ግን ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው አሥራትና መባዕ ለንስሐ አባትም ማለት ለካህናቱ ሆነ ማለት ነው፡፡ እንደውም በተጨማሪ በምእመናን ላይ እንዲከብዱ አያስፈልግም፡፡ ለካህናቱ ደመወዝ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ እየተከፈለ እንደገና ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ደመወዝ ከምእመናን መቀበል አያስፈልግም፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጣም የተጠነቀቀውና እንደ ትልቅ ነገር የሚያየው ለምእመናን አለመክበድን ነው፡፡ ሐዋርያ፣ የምእመናን አባት ሆኖ ለምእመናን መክበድ እንደማይገባ አስተምሯል፣ በተግባር አሳይቷል፡፡ ካህናት በምእመናን ላይ ከከበዱ ትልቅ ችግር ያስከትላል፡፡ ምእመኑ ሲከብደው ሸክሙ የሚቃለልበት ሌላ አማራጭ ይፈልጋል፡፡ ከቤተ ክርስቲያን መራቅና መሸሽም ይፈልጋል፡፡ ካህናት በምእመናን ላይ ሳይከብዱ በጣም ተጠንቅቆ በአግባቡ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ ደመወዝ ሳያገኙ፣ ሳያርሱ፣ ሳይነግዱ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ካህናት ከሆኑ ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን ማስተዳደር ስላለባቸው ምእመናን ሊረዷቸው ይገባል፡፡ አለበለዚያ ካህናቱ ከምእመናን ካላገኙ በስተቀር ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር በሌላ ሥራ ላይ ከተሠማሩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይጓደላል፡፡ ስለዚህ ሌላው ምእመን አርሶ፣ ነግዶ፣ ሠርቶ ከሚያገኘው ቤተ እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉት ካህናት የሚገባውን መክፈል አለበት፡፡ ይኸም በሰበካ ጉባኤ አማካኝነት ለቤተ ክርስቲያን መገልገያና ለካህናት ደመወዝ ይሰጣል፡፡

ደመወዝ የሌለው ካህን ከተገኘ ለሚያገለግለው ካህን እያንዳንዱ ምእመን አቅም ያለው በገንዘቡ በመደጐም በሌላም ነገር የሚረዳ አለ፡፡ ለምሳሌ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ካህናቱ ደመወዝ ስለሌላቸው ምእመኑ /የንስሐ ልጁ/ እርሻውን፣ አረሙን፣ አጨዳውን፣ ሌላውንም ሥራ በመሥራት የንስሐ አባቱን ይረዳል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለምሳሌ በጐጃም በዓመት አንድ ጊዜ በደብረ ዘይት ዕለት ስብሰባ ይደረጋል፡፡ በንስሐ አባት ቤት ጠበል ጸዲቅ ይዘጋጅና በዚያ የሚሰበሰበው የንስሐ ልጅ የተቻለውን ስጦታ ያደርጋል፡፡ በጎንደር በበጌምድር ስንሄድ የንስሐ ልጁ ካህኑን /የንስሐ አባቱን/ በእርሻ፣ በአረም፣ በአጨዳ በጉልበቱ ይረዳዋል እንጂ ካህኑ ከንስሐ ልጁ ገንዘብ አይጠብቅም፡፡ ምእመኑ ካህኑን በሚችለው አቅሙ ያገለግለዋል፡፡ ምእመኑ ለካህኑ ምንም ባያደርግለትም እንኳን ቄሱ የነፍስ አባት ነውና የንስሐ አባት ወይም መምህረ ንስሐ አልሆንህም አይለውም፡፡ ይህ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ካህን ሥዩመ እግዚአብሔር ነው፡፡ ምንደኛ አይደለም፡፡ ካህን ሹመቱ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስለሆነ በከንቱ ያገኘውን በከንቱ፣ በጸጋ ያገኘውን በጸጋ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

በሌላ በኩል እናትና አባት የሞቱባቸውን ችግረኛ ልጆች ማሳደግ፣ የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት አሥራት እንደ ማውጣት ሳይሆን የሚቆጠረው ብጽአት ነው የሚባለው፡፡ ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠው ራሱን የቻለ ነገር ነው፡፡ ከዚያ በተረፈ አንድ ሰው ለድሆች በየወሩ ወይም እንደተገኘ በሆነው ጊዜ መስጠት አለበት፡፡

በየቦታው እንደሚታወቀው ሕዝቡ ለድሆች ይሰጣል፡፡ አሥራትን ደግሞ ለሰበካ ጉባኤ ለብቻ ይከፍላል፡፡ ለተቸገሩ ሰዎች ይረዳል ይመጸውታል፡፡ አሥራቴን ለቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ከፍያለሁ ብሎ የሚለምነውን ድህ ዝም ብሎት አያልፍም፡፡ የሚችለውን ያህል ይሰጣል፡፡ ለድሆች የሚሰጠው የተለየ ነው፡፡ አንድ ሰው በየወሩ ከደመወዙ ወይም ከገቢው ላይ ለድሆች ይኸን ያህል እሰጣለሁ ብሎ ለይቶ መስጠት ወይም መክፈል ይችላል፡፡ ከአሥራቱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ለብቻ ማስቀመጥ ይችላል፡፡ ሕዝቡ ይህንን አሁንም እያደረገው ይገኛሉ፡፡ ድሀን ያበላል፣ ያጠጣል፣ ያለብሳል፡፡ ለተቸገረ ይሰጣል፡፡ ስለዚህ ከሰበካ ጉባኤ ውጪ ወይም ለቤተ እግዚአብሔር ከሚከፍለው ሌላ ለድሆች የተወሰነ ከገቢው ላይ ተምኖ በወር ይኸን ያህል እሰጣለሁ ማለት ይችላል፡፡ ሳይተምንም እንዲሁ በትሩፋት መስጠ ት ይችላል፡፡

## ነጋዴና ገበሬ አሥራት የሚያወጡት እንዴት ነው?

በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ይነሣሉ፡፡ ነጋዴ አሥራቱን የሚያወጣው ከዕለት ገቢው ነውን? ጠ ቅላላው ወጪውንና ገቢውን አስልቶ ትርፍና ኪሳራውን ካሰበ በኋላ ነውን? በዕለት፣ በወር ወይስ በዓመት? ገበሬውስ? የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች ይነሣሉ፡፡

ብዙ ጊዜ አሥራት፣ በኩራት ቀዳምያት ተብሎ ሲወጣ የኦሪት ሕግ ነው፡፡ በአጭሩ ከላይ እንደተገለጠው የወንጌል ሕግ ከዚህ በላይ ማድረግ ነው፡፡ የወንጌል ሕግ ደግሞ የተወሰነ ነገር አይሆንም፡፡ እንደውም በወንጌል አንድ ሰው ያለውን ሁሉንም ንብረት ሸጦ ገንዘቡን ለድሀ ሰጥቶ መመነንም አለ፡፡ የወንጌል ሕግ

የተለየ ነው:: በዚያን ጊዜ ለነጋዴ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ ነገር የለም:: የሆነው ሆኖ ግን ወደ ወንጌል ስንመጣ ነጋዴዎች ትርፋቸውን ቆጥረው ሂሳቡን አስልተው ተምነው አሥራት መስጠት ብቻ ሳይሆን ለቤተ እግዚአብሔር የሚገባውን ከሰጡ በኋላ በመባዕ ከዚያ በላይ መስጠት አለባቸው:: ገንዘባቸውን ቆጥረውና አስልተው ይኸን ያህል ገንዘብ ዕዳ አለብኝ ብሎ መክፈል አይደለም:: በወንጌል ይህን ያህል ገንዘብ የእግዚአብሔር ዕዳ አለብኝ፤ ይህን ዕዳ ልክፈል አይባልም:: ትሩፋት ነው መሠራት ያለበት:: ቤተ ክርስቲያንን ያሠራል፤ ይሠራል:: ድሆችን ይረዳል:: የፈለገውን መልካም ነገር ያደርጋል:: ለካህናትም የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል:: ባለው ገንዘብ ትሩፋት መሥራት አለበት እንጂ የተወሰነ ገንዘብ ቆጥሮ ይኸን ያህል የቤተ እግዚአብሔር ዕዳ አለብኝ ልክፈል አይባልም:: /1ቆሮ.16፥1-4፣ 2ቆሮ.9፥6-12/::

ስለዚህ በነጋዴው በኩል እግዚአብሔር ከሰጠው ገንዘብ ላይ በፈቃዱ መክፈል አለበት እንጂ ይህን ያህል ገንዘብ አለብኝ ልክፈል ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር የሚሰጠን ጸጋ ያልተወሰነ ነው:: እኛ ደግሞ እግዚአብሔር ከሚሰጠን ያልተወሰነ ጸጋ ወስነን አይደለም መስጠት ያለብን:: ከተሰጠን ሀብት ላይ ለእግዚአብሔር ባልተወሰነ ሒሳብ ወይም ተመን ትሩፋት መሥራት አለብን:: ዕዳዬ ይኸን ያህል ነው በማለት ተምኖ መክፈል የለበትም:: ወንጌል የትሩፋት ሕግ ነው::

ወደ ገበሬው ስንሄድ በኦሪቱ ሕግ አሥራት በኩራት ቀዳምያት ማውጣት አለበት:: በተመረተው እህል የመጀመሪያው ሥፍር ቀዳምያት ይባላል:: ያ የእግዚአብሔር ነው:: ከዚያ በኋላ የሚሠፈረው አሥር በሞላ ቁጥር አንድ ሥፍር ለቤተ እግዚአብሔር ይሰጣል:: አሥራት ነው:: በኩራት የሚባለው ደግሞ ከእንስሳት ሲወለድ የመጀመሪያው ለቤተ እግዚአብሔር ይሰጣል:: በእንስሳቱ በኩል በመጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ የሆነ /Cleaned/ እና ንጹሕ ያልሆነ /uncleaned/ አለ::

ንጹሕ ያልሆኑ ከሚባሉት እንስሳት /የጋማ ከብቶች/ የሚወለደው የመጀመሪያው እንዳለ ተወስዶ ለቤተ እግዚአብሔር አይሰጥም:: በገንዘብ ይዋጀውና ገበሬው ገንዘቡን ወስዶ ለቤተ እግዚአብሔር ይሰጣል::

ንጹሕ /uncleaned/ ወይም ቅዱስ የሚባሉት የተፈቀዱና የሚበሉት እንስሳት የመጀመሪያው ሲወለድ ለቤተ እግዚአብሔር ይሰጣል:: ቀዳምያት፣ አሥራት፣ በኩራት የሚባሉት ሦስቱን የሚመለከተው በኦሪት ሲሆን ገበሬውን ነበር:: በዚያን ጊዜ ሕዝቡም ኑሮው ግብርና ስለነበረ ነው:: ያን ጊዜ ሕዝቡ ማለት ገበሬው ነው:: ስለዚህ የገበሬው ሕግ ነው::

ወደ ሐዲስ ኪዳን ስንመጣ ግን አሥራቱ እንዳለ ተወስኗል:: ቀዳምያትና በኩራት የሚባሉት የሉም:: በዘመነ ሐዋርያት ሁሉም ያለውን ሀብቱን እየሸጠ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ገቢ እያደረገ በአንድነት መኖር የሚል ነገር ተጀምሮ ነበር:: በመጀመርያይቱ ቤተ ክርስቲያን ሀብቱን ሁሉ ሸጦ ለቤተ እግዝአብሔር አስገብቶ አብሮ መኖር ነበር:: ያ ሁኔታ አልዘለቀም:: በዚያው ተበትኗል:: ምክንያቱም ሕዝቡ እየበዛ ማኅበሩ እየሰፋ ሲሄድ ወደ 8000 ሲደርስ ችግር ተፈጠረ:: ማኅበሩም ተበተነ:: እናም ዋናው ትልቁ ነገር ለቤተ እግዚአብሔር ክፍያ የሚገባውን አሥራት መባዕ መክፈል ይገባል::

በሌላው አገር ስንሄድ የቤተ እግዚአብሔር ክፍያ የሚሰጠው በአብዛኛው በሙዳየ ምጽዋት ነው:: ሁልጊዜ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሙዳየ ምጽዋት ስጦታ አለ:: በየዕለቱ አገልግሎት የሚሰጥ የስእለት ስጦታም አለ:: በተለይ ከአሥር አንድ የሚለውን ስንመለከተው በሌላው አገር የለም:: እኛ አገር ግን አለ:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ ብቻ የብሉይ ኪዳንን ባሕሉን ትውፊቱን ይዛ ቆይታለች:: ሌላው ከአረማዊነት ወደ ክርስትና ሕይወት ነው የመጣው:: ባሕሉም የሌለውም:: ለቤተ እግዚአብሔር ትሩፋት የሚሰጡ፣ ብቻቸውን ቤተ ክርስቲያን የሚያሠሩ፣ ብቻቸውን የቤተ ክርስቲያንን ዓመታዊ በጀት የሚሸፍኑ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በተለያየ መንገድ ገንዘባቸውን በመባዕ በትሩፋት ይሰጣሉ እንጂ በርስት መልክ ይኸን ያህል መክፈል አለብኝ የሚለው ሁኔታ የለም:: ከላይ እንደተጠቀሰው እነሱ ከአረማውነት ወደ ክርስትና ስለ መጡ የኦሪቱ ባሕል የላቸውም:: እኛ ግን ከብሉይ ኪዳን ትውፊቱን ባሕሉን ይዘን ወደ ሐዲስ ኪዳን ስለ መጣን ሕገ ኦሪትንም ሕገ ትሩፋትንም አጣምረን ነው እየሄድን ያለነው::

እንግዲህ አሥራት ማውጣት ማለት ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ሲሆን ምጽዋት መስጠት ማለት ለድሆች፣ ለተቸገሩ፣ ለተራቡ፣ የሌላውን ርዳታ ለሚሹ፣ ተረጂ ለሆነው ወገን የሚያስፈልገውን ሃይማኖታዊ፣ ሰብአዊ ርኅራኄያዊ የሆነውን ሥራ መሠራት ርዳታ ማድረግ ማለት ነው:: ለድሆች የሚሰጠውን አሥራት ምጽዋት ልንለው አንችለም:: ለቤተ እግዚአብሔር የሚሰጠውንም ምጽዋት አንለውም::

## ለሰበካ ጉባኤ በዓመት ብር 12 ወይም ብር 24 የሚከፈለው አሥራት ይባላል?

ስለ ወርኃዊና ዓመታዊ አስተዋጽኦ በቃለ ዓዋዲው «አንቀጽ 56 ቁጥር 1/ሀ «ገቢ ያለው ካህንም ሆነ ምእመን ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን አስተዋጽኦ /አሥራት/ ብር ከአንድ ብር እስከ ሁለት ብር፤ በዓመት ከአሥራ ሁለት ብር እስከ ሃያ አራት ብር ይከፍላል።» ይላል። ቃለ ዓዋዲው ይኽንን ያስቀመጠው በአሥራት አንጻር ቀርጾ ነው። ደንቡ የሚለው ከአሥር አንድ ነው። የሕዝቡን ኑሮና አቅም በማገናዘብ ነው እንጂ ሙሉ በሙሉ ከአሥር አንድ የሚከፈል ተደርጎ አልተቀመጠም። የቻለ ግን ከገቢው ከአሥር አንዱን ሙሉ በሙሉ መክፈል ይችላል። መጀመሪያ ርትዑን አሥራ ሁለት ብሩን ወይም ሃያ አራት ብሩን ከከፈለ በኋላ ለቤተ እግዚአብሔር ከዚያም በላይ ማድረግ አለብኝ ብሎ ካደረገ ትሩፋት ነው።

አሥራት የሚከፈለው ለሰበካ ጉባኤ በደረሰኝ ብቻ ነው? ወይስ ሙዳየ ምጽዋት ውስጥ ይከተታል? ሙዳየ ምጽዋት በኦሪቱም ጊዜ ነበር። እርግጥ ሁለቱ የተለያየ ነው። ሙዳየ ምጽዋት በአብዛኛው በወንጌለ ባሕል አንጻር ነው። አሥራት ግን በደረሰኝ የሚከፈል ርትዕ ነው። በአደባባይ ተከፍሎ በሥነ ሥርዓት በደረሰኝ ገቢ የሚደረግ ነገር ነው።

## ሳይከፈል የቆየ አሥራት

ሳይከፈል ብዙ ገዜ ያለፈበትንና የተጠራቀመውን አሥራት ለመክፈል፤ አቅመ ያለው ሰው መክፈል ይችላል። ድሀው ግን አይችልም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ላይ የተቸው ጉዳይ ነው። ድሆች ከሆኑ እንደውም ውዝፉን መክፈል ቀርቶ የወቅቱንም እንኳን ከአቅማቸው በላይ ከሆነ መገደድ የለባቸውም። ለእግዚአብሔር ዋናው ነገር ትርፉ ገንዘቡ አይደለም። ምሕረቱና ቸርነቱ ነው። በእርግጥ ድሀ ነኝ እያለ አሥራቱን ከመክፈል እንዲርቅ አይደለም። ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። አቅማቸው የማይፈቅድላቸው ድሆች ግን አሥራት መጠየቅ የለባቸውም። ሳይሠሩ ቁጭ ብለው የሚውሉትን ሰነፎች ሳይሆን እነሱ ወጥተው ወርደው ራሳቸውን ችለው ካደሩ እግዚአብሔርን አገለገሉ ማለት ነው። የሀብትን ንብረት መጠንን በመቁጠር ሳይሆን በጥረቱ የዕለት ኑሮውን አሸንፎ በደንብ የሚያድር ሆኖ ከተገኘ እርሱ ድሀ አይባልም። ድሀ የሚባለው ያቺኑ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ የሚቸገር የሚራብ የሚታረዘው ነው። የዚህ ዓይነቱ ርዳታ ያስፈልገዋል እንጂ የወቅቱንም ሆነ የተጠራቀመብህን ውዝፍ አሥራት ሳትበላ ሳትጠጣ ራቁትህን ሳለህ ለቤተ ክርስቲያን ክፈል አይባልም።

በየገጠሩ ያሉ የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት

የመንግሥት ሠራተኛውም ሆነ ነጋዴው በአብዛኛው ያለው በከተማ ነው። አሥራቱን ለሚገለገልበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያውጣ ከተባለ በርቀት በየገጠሩና በየጠረፉ ያሉ የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናትን እንዴት መርዳት ይቻላል? የሚል ጥያቄ አለ።

በአጥቢያ ከዚያም አልፎ በአገር ዓቀፍ ደረጃ ያለውን ችግር እያንዳንዱ ምእመን በተናጥል ሊፈታው አይችልም። ማዕከላዊ አሠራር ሊኖረው ያስፈልጋል። እያንዳንዱ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማዕከል አለው። በወረዳ ከዚያም በሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና አለን። ወደ ላይ በየደረጃው እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ ድረስ አለ። ጠቅላላው ገቢ ከእያንዳንዱ ምእመን በአጥቢያ ደረጃ ከተሰባሰበ በኋላ ያንን በማስተንተን ማብቃቃት ነው። አሁን ያለው ችግር በአንዱ ቤተ ክርስቲያን የተትረፈረፈ ብዙ ገቢ ሲገባ ሌላው ደግሞ የዕለት መቀደሻ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ አጥቶ ሲቸገር ይታያል። የቤተ ክርስቲያንን ገቢ በአግባቡ ለመጠ ቀም በሚገባ የተደራጀና የተጠናከረ ማዕከላዊ አሠራር ቢኖር ይሄ ችግር አይፈጠርም ነበር። ምእመናን አሥራታቸውን ራሳቸው ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰጡ ያደረጋቸውም ይኸው ነው።

እንዲህም ሆኖ ግን በግለሰብ ደረጃ ገንዘብ ያለው ባለ ጸጋ ምእመን ከአጥቢያው አልፎ በየገጠሩ የሚገኙትን ገዳማትና አድባራት በሚገባ እየረዳ ነው። በቡድን በኅብረት እየሆኑ በየገጠሩ በየጠረፉ ያሉትን የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት የሚደገፉ፣ የፈረሰውን የሚጠግኑ፣ አዲስ የሚያሠሩ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይጓደል የሚያደርጉ ምእመናን በርካታ ናቸው። ታላቅ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ።

ስለዚህ ምእመናን በአጥቢያቸው የሚከፍሉት አሥራት ሌላውን የትሩፋት ሥራ እንዳያደርጉ አይከለክላቸው። በአጠቃላይ ግን ምእመናን በተናጠል የሚያደርጉት ርዳታ የሁሉንም ደሀ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ችግር ሙሉ በሙሉ አይቀርፍም። መሠረታዊ መፍትሔ የሚኖረው በማዕከላዊ ሁኔታ በተቀነባበረ መልኩ በድርጅታዊ አሠራር ነው። ይህንን ሁኔታ ምእመናንና ካህናቱ በቤተ ክህነት አማካኝነት በሚገባ ተወያይተውበት ቢወስኑ ማዕከላዊ አሠራር ለማምጣት አያስቸግርም ነበር። ካህናቱና ምእመናን በዚህ ጉዳይ ላይ መቀናጀት አለባቸው። ቤተ ክህነት ለምእመናንና ለካህናቱ በጉዳዩ ላይ ከአጥቢያ አንሥቶ የቤተ ክርስቲያንን ገቢ በማዕከላዊ ሁኔታ በሥርዓት ለመምራትና ለማስተዳደር ተከታታይ ዐውደ ትምህርት በመስጠት ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ካህናትና ምእመናን ጭምር አብረው በጋራ እንዲወስኑ ከተደረገ መልካም ነው። ካህናቱም በአብዛኛው ይኽንን ነገር የሚደግፉት

ሐሳብ ይሆናል። በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ገቢ ሥርዓት ባለው ሁኔታ በአግባቡና በማዕከላዊ አሠራር ሆኖ የተዘጉና የተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት ጭምር በማዕከል ደረጃ እንዲደጐሙ ይሁን ተብሎ ሐሳብ ቢቀርብ የእያንዳንዱ አጥቢያ ምእመን የሚቀበለው ጉዳይ ነው።

## ምእመናን አሥራታቸውን በአግባቡና በወቅቱ እንዲያወጡ ምን መደረግ አለበት?

ይህን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ አለ። ሕዝቡ የባሕል ግጭት አለበት። ችግሩ የባሕል ግጭቱን ማስታረቅ አለመቻላችን ነው። የባሕል ግጭቱ ምንድ ነው? በተለይ በቀጥታ አሥራት የሚለው ነገር በመጽሐፍ ቢኖርም በተግባር በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲሁም በከተማው አልታየም።

ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያን በጣም ብዙ ነገር ያደርጋል። በአሥራት መልክ ለሰበካ ጉባኤ እንዲከፍል ሲጠየቅ ግን እንደ ትልቅ ዕዳ አድርጐ ይመለከተዋል። በግድ ነው የሚከፍለው። ምክንያቱም ልምዱ ከሥር ጀምሮ እየዳበረ ስላልመጣ ነው። ይሁን እንጂ ሕዝቡ ለቤተ ክርስቲያን ከአሥራ ሁለት ብር እና ከሃያ አራት ብር በላይ የበለጠ ብዙ ያደርጋል። ይህችኛዋ አዲስ ሕግ ሆና ስለ መጣችባቸው እንደ ትልቅ ዕዳ ይቆጥሯታል። ለቤተ ክርስቲያን ሲረዱ፣ ንዋያተ ቅድሳቱን ሲያሟሉ፣ አዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሲሠሩ፣ የፈረሰውን ሲጠግኑ፣ ድሀ ሲረዱ፣ ሲዘክሩ፣ ሲጋብዙ፣ ሲያለብሱ እጅግ ብዙ ነገር ሲያደርጉ አሥራት ከሚከፍሉት በላይ ያወጣሉ። ነገር ግን በዓመት የተወሰነውን አሥራት መክፈል ይከብዳቸዋል።

አሁን ከጊዜ በኋላ የከተማው ሰው እየለመደው የመጣ ይመስላል። በአብዛኛው የገጠሩ ሕዝብ ግን በባሕለ ማርያም ባርኪ ተብሎ በየውድማው የመሪጌታ ይከፍላል። የገበዝ ይከፍላል። የዓመት መቀደሻ ይከፍላል። በተለይ በጉራጌ ማኅበረሰብ በአካባቢው ደብር የሚቀደሰው የዓመቱ በዓል ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ተለይቶ የሰበካው ሕዝብ አዋጥቶ የዓመት አስተዋጽኦ ይሰጣል። ከዚያ በተረፈ ደግሞ ራሱ እያወጣ መገበሪያ ይሰጣል። ይኸን እያደረገ አሥራት ለብቻ ክፈል ይባላል። ያንን ሁሉ እያደረገ አሥራት ክፈል መባል የለበትም።

ለማርያም ባርኪኝ፣ ለመሪጌታ፣ ለገበዝ ለመቀደሻ ወዘተ በእህል መልክ የሚሰጠውን በሰበካ ጉባኤ ሒሳብ በአሥራት መልክ መያዝ ይቻላል። ከዚያ በኋላ በተለያየ ምክንያት መጠየቅ የለበትም። የተሰበሰበውን ለሚፈለገው ነገር በአግባቡ በሥርዓት እያወጡ መመደብ በሚገባ መጠቀም ይቻላል። ሕዝቡ የተሰበሰበው እህል በሰበካ ጉባኤ ገቢ ተይዞ በሚገባ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ላይ ሲውል ማየት አለበት። በገጠር ገበሬው በየዓመቱ ምርቱን በውድማ በሚሰበስብበት ጊዜ የሚሠፈረው በቃል ዓዋዲው እንደ አሥራት የሰበካ ጉባኤ ክፍያ ሆኖ ሊመዘገብለት ይገባል። ደንቡ የሚለው ይኸንን ነው። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ይህንን በአግባቡ ተግባራዊ የሚያደርገው ስለሌለ ግጭት ሲፈጥር ይታያል። ይህንን ለማስተካከል ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በየሀገረ ስብከቱና በየወረዳው በሴሚናር መልክ በማስረዳት ግንዛቤ እንዲፈጠር እንደተደረገው ሁሉ ወደፊትም በተጠናከረ ሁኔታ መቀጠል ይኖርበታል። ስብከተ ወንጌልም ተጠናክሮ ከተስፋፋ ምእመናን አሥራታቸውን ለምንና እንዴት ማውጣት እንዳለባቸው እየተረዱት ከእነሱ የሚጠበቅባቸውን በጊዜው ለማድረግ ይነሣል።

### ማጠቃለያ

በየትኛውም ዓለም የሚኖረው የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ምእመን ሁሉ ከአጥቢያ ጀምሮ እስከ ማዕከል ያለችውን ቤተ ክርስቲያን አንድ አድርጐ ማየት ይገባዋል። የገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን አለመኖር ማለት ማዕከላዊው የቤተ ክርስቲያን አካል አለመኖር ማለት ነው። ዳሩ ሲፈታ መሐሉ ዳር ይሆናል ይባላል። በእኛ በቤተ ክህነትም በምእመናንም ዘንድ ይህንን ተረድተንና አምነንበት የገጠሯ ወይም በጠረፍ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ስትዘጋ በዝምታ ማየት የለብንም። ያቺ ከዳር ያለችው የገጠር ቤተ ክርስቲያን ስትዘጋ መሐሉም ዳር እንደሚሆን አውቀን በጠቅላላው ምንም ገቢ የሌላቸውን አብያተ ክርስቲያናት በችግር ምክንያት እንዳይዘጉ ማድረግ አለብን።

ለዚህ የተሻለው መፍትሔ የቤተ ክርስቲያንን ገቢ በማዕከላዊ ሁኔታ አደራጅቶ በሥርዓት በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ነው። ሌሎች አገሮች የሚያደርጉት እንደዚህ ነው። በአንዱ ገቢ ነው ሌላው አነስተኛ ገቢ ያለው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚተዳደረው። በአንዱ አጥቢያ ያለ ምእመናን ቁጥራቸው አነስተኛ ሆኖ በሌላው አጥቢያ ብዙ ሺሕ ምእመናን ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ በጠረፍ አካባቢ ሃያና ሠላሳ ምእመናን ይኖራሉ። እነዚያ በአነስተኛ አቅማቸው ካህን ቀጥረው መገልገልና ማስገልገል ስለሚያቅታቸው ቤተ ክርስቲያኑም ይዘጋል። እነርሱም ወደ አረማዊነት ይመለሳሉ። በአንዱ አጥቢያ

እጅግ የተትረፈረፈ ሀብት በአንድ በኩል ደግሞ ባዶ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህን አስተካክለን በገጠሯ ቤተ ክርስቲያን ጭምር አገልግሎቱ ሳይጓደል የሚሰጥበት ሁኔታ ቢኖር መልካም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ለማድረግ አቅሙም ችሎታውም አላት፡፡ ያጣነው ዘዴ ብቻ ነው፡፡ መቀናጀት ያስፈልጋል፡፡ ምእመናን ካህናትና በየደረጃው ያሉ የቤተ ክርስቲያን አካላት በቅንጅት በመወያየትና በጋራ በመሥራት የቤተ ክርስቲያናችንን የተጠናከረ አሠራር እግዚአብሔር እንዲያሳየን እንመኛለን፡፡